# ለአይኢፒ ስብሰባ መዘጋጀት

## የቤተሰብ መመሪያ

**ለአንድ ሰው የተዘጋጀ የትምህርት መርሃ ገብር (አይኢፒ) ስብሰባዎች የተማሪያችሁ ልዩ ትምህርት ልምምድ ወሳኝ አካል ናቸው። እነዚህ ስብሰባዎች ለተማሪያችሁ ግቦች፣ ድጋፎችና አገልግሎቶች በመቅረጽ ሂደት ውስጥ እናንተን ለማካተት የተዘጋጁ ናቸው። ተማሪያችሁን ሙሉ በሙሉ እና በብቃት እንድትደግፉ ለመዘጋጀት ስለሚረዳችሁ ይህንን መመሪያ ተጠቀሙ።**

## በመጀመሪያ ደረጃ:- ሰነዶቻችሁን አሰባስቡ

**ልዩ ትምህርት ብዙ የወረቀት ስራ ይፈልጋል። ከተማሪያችሁ የአይኢፒ ስብሰባ በፊት ያለፈው ዓመት ሰነዶቻቸውን በሙሉ በመዳሰስ ሁሉንም ነገር እንዳላችሁ ለማረጋገጥ ጊዜ ውሰዱ። እነዚህ ሰነዶች የሚከተሉትን ያካትቱ ይሆናል**

- [ ] **ረቂቅ አይኢፒ እና ሌላ የስብሰባ ሰነዶች:-** የአይኢፒ ረቂቅ እና በስብሰባው ላይ ውይይት የሚደረግባቸው የትኞቹም ሌሎች ሰነዶች ቅጂ ከስብሰባው ቢያንስ 5 ቀናት በፊት ሊደርሳችሁ ይገባል።

- [ ] **ሪፖርት ካርዶችና የሚታይ የለውጥ መከታተያ:-** የተማሪያችሁ በጣም የቅርብ ጊዜ ሪፖርት ካርድ እና/ወይም የለውጥ መከታተያ ማግኘታችሁን አረጋግጡ። ይህ የአይኢፒ ለውጥ መከታተያ፣ ከመምህራን የለውጥ መከታተያ ወይም የልጃችሁ ትምህርት ቤት የሚገለገልበት ኦንላይን የመማሪያ መርሃ ግብሮች የለውጥ መከታተያ (ኤስቲ ማት፣ አይሬዲ ...ወዘተ) ያካትታል።

- [ ] **ማህበረሰብ ተኮር ሰነዶች:-** ተማሪያችሁ ላይ የሰሩ እንደ የህጻናት ሀኪም፣ ሞግዚት ወይም እንደ የአካላዊ ቴራፒስት ወይም የክሊኒክ ማህበራዊ ሰራተኞች ያሉ የውጪ አገልግሎት ሰጪዎች ካሉ ማህበረሰብ ተኮር ባለሙያዎች ላይ ከቀደሙ ዓመታት የተሰበሰቡ የትኞቹም የምርመራ፣ የመከታተያ፣ ወዘተ ሰነዶች ቅጂዎች ማግኘታችሁን አረጋግጡ።

- [ ] **የስራ ናሙናዎች:-** ልትናገሩበት በምትፈልጉት ጉዳይ ዙሪያ የስራ ናሙናዎች አሰባስቡ። እንዲህ ዓይነቱ ስብስብ ዋናዋና ተሰጥተው የተሰሩ ስራዎች ይመለከተኛል የምትሏቸው ምሳሌዎች የሚያሳዩ ተሰጥተው የተሰሩ ስራዎች (የፊደል ግድፈቶች፣ የማካፈል ተግዳሮቶች፣ የእጅ ጽኹፍ መደናቀፎች...... ወዘተ) ሊያካትት ይችላል።

> **ፍንጭ:- ዓመቱን ሙሉ በጥንቃቄ አሰባስቦ ለማስቀመጥና ከአይኢፒ ስብሰባ በፊት እነዚህን በማሰባሰብ ጊዜ ከመግደል ስለሚያድናችሁ ለእነዚህ ሰነዶች ሁሉ ማህደር ወይም የኮምፒዩተር ፎልደር ይኑራችሁ!**

## በሁለተኛ ደረጃ:- መከለስ እና ማስታወሻ መያዝ

**አሁን እነዚያን ሁሉ ሰነዶች አሰባስባችኋል። እያንዳንዱን መልሳችሁ ለማየት እና ዋና ዋና ነጥቦችን ለማስታወስ ለይቶ ለመጻፍ ጥቂት ጊዜ ውሰዱ። ማብራሪያ የምትፈልጉበት ወይም በግንኙነቱ/በስብሰባው ልትወያዩበት በምትፈልጉት የትኛውም ጉዳይ ላይ ከስሩ ማስመራችሁ ወይም በቀላሉ እንዲታያችሁ ቀለም መቀባታችሁን እርግጠና ሁኑ። በዚህ ደረጃ እነዚህን ሰነዶች ስትዳስሱ ከእናንተ ጋር ሰነዶችን በመዳሰስ ለማገዝ የዲሲ ልዩ ትምህርት መረብ ደስተኛ ነው!**

# በሶስተኛ ደረጃ:- ያላችሁን ጥያቄዎችና አስተያየቶች ጻፉ

**ቀደም ብላችሁ ጥያቄዎቻችሁና አስተያየቶቻችሁ ጽፋችሁ መያዛችሁ ምንም ዓይነት ጠቃሚ ነጥብ አለመርሳታችሁ ለማረጋገጥ ይጠቅማችኋል ወይም በግንኙነቱ ጊዜ ቦታው ላይ ለመናገር ዝግጁ መሆናችሁን ያሳያል። ከዚህ በታች ጥቂት ለመነሻ የሚሆናችሁ ሀሳብ ቀርቦላችኋል።**

### ነገን ማለም

- በሚቀጥለው ዓመት መጨረሻ ተማሪዬ ብቁ እንዲሆንባቸው የሚያስፈልጉት ሶስት እጅግ ጠቃሚ ክህሎቶች ምንድን ናቸው? በእነዚህ ግቦች ላይ እንዴት ይንጸባረቃሉ?
- መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/ምርቃት/.... ወዘተ ለማቀድ መቼ ይጀምራሉ?

### የማብራሪያ ጥያቄዎች

- የአይኢፒ ረቂቅ _____________. እንደሚል ተመልክቻለሁ። ስለዚህ ጉዳይ የበለጠ ልትነግሩኝ ትችላላችሁ?
- የአይኢፒ/የዳሰሳ/ ... ወዘተ
- ______________. የሚልይመስለኛል። ልክ ነው?ይህን በተለየ መንገድ ልታብራሩት ትችላላችሁ?

### በጥንካሬ የተለዩ

- ____________እቤት ውስጥ በጥሩ ሁኔታ እንደሰራ አስተውያለሁ። ትምህርት ቤት ውስጥስ ተመሳሳይ ስልቶች እንዴት ልንጠቀም እንችላለን?
- እዚህ ላይ ብዙ መሻሻሎች አስተውያለሁ ተማሪዬ ስኬታማ እንዲሆን ምን ዓይነት ስልቶች እረዱት? እነዚያን ስልቶች በሌሎች ጉዳዮች ላይ እንዴት ልንጠቀም እንችላለን?
- ተማሪዬ በእውነት ለ ___________. የተለየ ፍቅር አለው። እነሱን ለመደገፍ ለማገዝ ያን ፍላጎት እንዴት እንጠቀመዋለን?

### አገልግሎቶች እና መገልገያዎች

- እነዚህ መገልገያዎች እንዴት የተማሪዬን ፍላጎት ያሟላሉ?
- ይህ ከባቢ ለተማሪዬ ለምን ምርጡ ከባቢ ሆነ? _____. የሚሰጠው ድጋፍ ሊታየኝ አልቻለም።
- እነዚያ ፍላጎቶቸ ያሉት ተማሪዬ እንዴት እንደግፈዋለን?
- ተማሪዬ ይህን ያህል ድጋፍ እንደሚያስፈልገው እርግጠኛ አይደለሁም። ሌላ ምን ማድረግ እንችላለን?

### ፍላጎት መግለጽ

- ጥልቁ ክፍተት _________. እንደሆነ አይቻለሁ። እንዴት እናሟላቸዋለን?
- ይህ ግብ በበቂ የተዘረዘረ አይመስለኝም። ለተማሪዬ ፍላጎት የበለጠ የተወሰነ ለመሆኑ እንዴት እርግጠኛ መሆን እንችላለን?
- ይህ ከሁሉ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ አይመስለኝም። ተማሪዬን የበለጠ የሚጠቅመው ሌላ ምን ላይ ማተኮር እንችላለን።
- ከቅርብ ግዜ ወዲህ የ ________ አካሄድ አሳስቦኛል። ምን አገልግሎትና ድጋፍ በዚህ ጉዳይ ላይ ሊያግዝ ይችላል።


(202) 671-2890

specialeducation.dc.gov

specialeducation@dc.gov

@specialeducationdc

DC SPECIAL EDUCATION HUB

# አራተኛ ደረጃ ፡- ሌሎች መብቶቻችሁን እወቁ

**የሚከተሉት መብቶች ያሏችሁ ቢሆንም ትምህርት ቤቱን እንደ ተርጓሚ ያሉ የተወሰኑ ነገሮች አስቀድሞ እንዲያቀርብ ልትጠይቁ ትችሉ ይሆናል።**

- ☐ **በዋናነት በምትነጋገሩበት ቋንቋ የጽሑፍ ሰነዶች፡-** እናንተ ምንም ወጪ ሳታወጡ ብሬልን ጨምሮ በደንብ በምትነጋገሩበት ቋንቋ ሁሉም የጽሑፍ ሰነዶች ተዘጋጅቶ የማግኘት መብት አላችሁ።
- ☐ **ተርጓሚ፡-** እናንተ ምንም ወጪ ሳታወጡ በደንብ በምትነጋገሩበት ቋንቋ ኤኤስኤል ጨምሮ ለአይኢፒ ስብሰባ ተርጓሚ የማግኘት መብት አላችሁ።
- ☐ **ሌሎችን መጋበዝ፡-** ጠበቃ፣ የህግ ባለሙያ፣ ከልጃችሁ ላይ የሚሰራ የውጭ ባለሙያ፣ የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ በአይኢፒ ስብሰባ ላይ እንዲያግዛችሁ የመጋበዝ መብት ያላችሁ ሲሆን ትምህርት ቤቱ ማን ስብሰባው ላይ እንደሚገኝ አስቀድማችሁ አሳውቁ።
- ☐ **በርቀት መከታተል፡-** ከሩቅ በስልክ ወይም እንደ ዙም ባሉ ዘዴዎች የቪዲዮ ጉባኤ ስብሰባውን የመከታተል መብት አላችሁ - አስፈላጊ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በእነሱ በኩል መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ እንዲችሉ እናንተ በዚህ መንገድ የምትሳተፉ ከሆነ አስቀደማችሁ ለትምህርት ቤቱ አሳውቁ።
- ☐ **የአሰራር ጥንቃቄ ማሳወቂያ፡-** እንደ የልዩ ትምህርት ተማሪ ወላጅ መብታችሁን ዘርዝሮ የያዘው የአሰራር ጥንቃቄ ማሳወቂያ ቅጂ የማግኘት መብት አላችሁ። እነዚህን የቨርቹዋል ሰነዶች እና/ወይም በሀርድ ኮፒ ለማግኘት ልትጠይቁ ትችላላችሁ።
- ☐ **ስብሰባው መቅረጽ፡-** ስብሰባውን ለመቅረጽ መብት አላችሁ ግን አስቀድማችሁ ለትምህርት ቤቱ መንገር አለባችሁ።

**ፍንጭ፡- ተርጓሚ፣ተጨማሪ የሰነድ ቅጂ ... ወዘተ የምያስፈልጋችሁ ከሆነ ማንን ማናገር እንዳለባችሁ እንደምታውቁ አረጋግጡ። ይህ የልጃችሁ ጉዳይ ስራ አስኪያጅ፣ የልዩ ትምህርት አስተባባሪ፣ ወይም ሌላ የስራ ባልደረባ ሊሆን ይችላል። በአመቱ መጀመሪያ ላይ አስቀድማችሁ የግንኙነት መረጃ ያዙና እንዴት እንደምትገናኙ ታውቃላችሁ።**

# በአምስተኛ ደረጃ፡- ዝርዝሩን አመሳክሩ

**ልታጠናቅቁ ነው! በአይኢፒ ስብሰባ ሳምንት የመጨረሻው ቃለ ጉባኤ ዝርዝር በሙሉ ለማረጋጥ ትምህርት ቤቱ እንደሚደርሱ እርግጠኛ ሁኑ!**

- ☐ **የስብሰባ ቦታ፡-** ስብሰባው በአካል ተገናኝቶ ነው? በትክክለኛ ቦታ ላይ መድረሴን ለማረጋገጥ ትምህርት ቤቱ ስደርስ ምን ማለት ይኖርብኛል? ስብሰባው በርቀት ከሆነ የትኛው መገኛ/የስልክ ቁጥር እጠቀማለሁ?
- ☐ **ተሳታፊዎች፡-** በዛ ስብሰባ የሚሳተፈው ማን ነው? የትኞቹ መምህራን ይገኛሉ? ስብሰባው ላይ ካልተገኙ ከሌሎች መምህራን መረጃ እንዴት ታገኛላችሁ?

**ፍንጭ፡- ትፋሻችሁን ሰብስቡ - እዚህ ደርሳችኋል! ስለ አይኢፒ ስብሰባዎች ወይም በዲሲ ውስጥ ልዩ ትምህርት ተጨማሪ ጥያቄዎች አሏችሁ? ለተጨማሪ ድጋፍ የዲሲ ልዩ ትምህርት መረብን አነጋግሩ!**

(202) 671-2890
specialeducation.dc.gov
specialeducation@dc.gov
@specialeducationdc
DC SPECIAL EDUCATION HUB